# አንድነት

የኃይላችን መደብር
የሕዝብ ዝሃ መዘውር
ከዚያም ከዚህ ድር ሲያብር
የጠላት ነብስ የሚሰውር
ወልጋዳ ሥርዓት የሚሰብር።

አንድነት የዲሞክራሲ ውጋግራ
ለተከፉት መከታ ለፍትሃቸው ጣራ
የቆራጥ ጀግና አዝመራ ለተራቡት ጎተራ
ለጎጠኞች አንጀት ቆራጭ ለድግምቶች ደብተራ
በሩቁ የሚሰማ ለጠላት የሚያስፈራ።

የፍቅር ጽዋ አቃማሽ
የሃይል ሸማ አላባሽ
የጠባቦች እዝምት አፍራሽ
ለተበደሉት ፈጥኖ ደራሽ
የሰላም ሁሉ አዳራሽ የፈለግነውን አስመላሽ።

ተሞሻሪ ጮሌዎችን አስወግዶ
የትግል ጭላቶችን በወፈንጠር ቀይዶ
የሙታን ቁራን አሳዶ
የተለጣፊ ጎራን አስደግድጎ
ከንቱ አጫፋሪን አስወግዶ
የጠነዛውን ሥርዓት አቆራፍዶ
ትብብር መምጽአት ተጸንሶ ጀግና በምጥ ተወልዶ
እንቡጥ አርበኛ ስር ሰዶ
ፍትህ ያነግሳል በጨቋኞች ላይ ፈርዶ።

አንድነት የመብት ባላንጥነት
የህዝብ ስልጣን ባለቤት
የትግላችን ኃዋርያ የደስታችን ማህሌት
የጥንት አባቶች ቅኝት የእናቶቻችን ስሪት
ታላቅ ኢትዮጵያዊነት ለታጠቀ ኃይል ጉለበት
ክቡር አፍሪቃዊነት የጥቁር አርያነት
የነ ሉሲ ተወላጆች የትውልድ ሃረግ ባለበቤት

የዓለም ዘር ሁሉ መነሻ የጽዮን ማረፊያ ቤት።

አንድነት የጡንቻችን ፍረጣሜ
የጉግ ማንጉግ ድምዳሜ
ለዘረኞች የሞት መርዶ የቀብራቸው ፍጻሜ
የወያኔ ጥቁር ከፈን የመጨረሻው ስያሜ።

አንድነት ላጥፊ ጎጠኞች ስለት
ላረጀው መንግስት ውድቀት
ላረንቋው ሥርዓት ድርቀት
ለአንባገነኖች ቅስፈት
ለአዲሱ ትውልድ ምህረት።

አንድነት የቃል ኪዳን ቀለበት
የኢትዮጵያውያን ዘለበት
የጥንት ጀግኖች አዝማችነት
የብሄሮች እኩልነት
የቋንቋወች ብረቅነት
የባህላችን ወርቅነት የታሪካችን ብቁነት
የዜግነት አርማችን የህልውና ሰብነት።

አንድነት የመቻቻል ሰንደቃችን
የጥንካሬ አርማችን የነጻነት አላማችን
የስልጣን ሽሚያ ማረሚያችን
ያጎብዳጆች መምቻችን
የክፍፍል መፍትሄአችን ለህዝባዊ ሥርዓታችን
ለመጨረሻው ግባችን ጽኑ መሰረታችን።

አንድነት የትግል አቡጊዳ ያቋማችን መከዳ
የትብብር ናኩተከ የድርጅቶች አኮፋዳ
በመፈክር አሃዱነት ጠላትን የሚነዳ
አስተማማኝ የጦር ሜዳ የውይይት ሰሌዳ
ለጭቁኖች መውዜር ለዘረኞች ፍዳ።

አንድነት የታገዮች ስይመት
አርማ አንጋቢ በህዝብ እምነት
የቆራጥ ትውልድ እድመት
የጀግና ልጆች ዋቢነት
ለተማመኑ ዝክረት ለገዥዎች ሹም ሽረት
ለከፋፋዮች እፍረት ለከሃዲዎች ውርደት

ለህያው አርበኞች ድፍረት
ለህዝብ ቅንጂት ብረት ለፓርቲዎች ህብረት
ለታሪክ ማህደር እውነት
ለአንባገነኖች ሽንፈት።

አንድነት የመልካችን ወርቀ ማህለቅ
የሃይማኖት መቻቻል የጋራ ኑሮ ሰንደቅ
ወገን ሲደነቅ መሰሪ ጠላት ሲጨነቅ
አምባገነን ሲብረከረክ ውስጥ ሴረኛ ሲንቦጫረቅ
ባጉል ስራው ሲሸማቀቅ በጀግና አርበኛ ሲጨፈለቅ
ሳይወድ በግድ ለህዝብ ስልጣን ሲለቅ
ዘረኛ ህግን በዲያብሎስ ሲነጠቅ
የጀግና ሙታን ሲጸድቅ።

አንድነት የፍቅራችን ሰንሰለት
የህዝባዊ ትግል ስምረት
የውድ ኢትዮጵያ ጸሎት
የጥንት አባቶች ውርሰት
የዳር ደንበር አለኝታ የታሪክ ምስክርነት
ለጭቁኖች አንደበት ለተሰውት ህያውነት።
አንድነት ከቀይ ባህር እስከ ቦረና
ከሃረር እስከ ብቸና በላይ በአባይ ጣና
ከራስ ዳሽን እንዳባጉና
ከዋልድባ እስከመና
በነዘራይ የጀብድ ዝና
በነአባ ጅፋር ጎዳና
በነካሳ ቆራጥ ፈለግ በነባልቻ የጦር ጀግና
ኢትዮጵያችን ኢትዮጵያ ሁና በክብር ቀስተ ደመና
በነኩሽ ቅዱስ መሬት በኖህ ዘመን መዲና።

ከዳንኤል ጎበዜ